አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 53

የካቲት 12 ቀን 2015 (19-02-2023)

ጊዜው በጨመረ ቁጥር ያገራችን ፈተና እየጨመረ መጣ እንጂ አልቀነሰም፣የሕዝቡም እልቂትና መከራ እንደዚያው።ባለፈው ሳምንት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ በአቡነ ማቴያስ በተመራው ሲኖዶስና የኦሮሙማው መሪ በሆነው አብይ አህመድ ባዋቀረው ሕገወጥ የኦሮሙማ ፓትሪያርክና ጳጳሳት መካከል ተደረሰ የተባለው ስምምነት የጊዜ መግዣ እንደሆነ በወቅቱ መግለጻችን ይታወቃል።ያልነው አልቀረም፤ ከዚህ ቀደም አጼ ክህደቱ ብለን የሰየምነው አብይ አህመድ ላባቶች የገባውን ቃል ጥሶ እግራቸው ገና የቤተመንግሥቱን ግቢ ሳይሻገር በኦርቶዳክስያኑ ላይ የወከባና አፈሳ ተግባሩን ባዘጋጀው የኦሮሙማ የታጠቀ አሸባሪ ቡድን ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክሮ መቀጠሉን፣የሕዝቡንም አልበገሬነት ያዬንበት ሰሞን ነው።

ከስርዓቱ ባለሥልጣኖች ጀምሮ የሁሉም የማህበር ክፍሎችን፣ ሙስሊምና ፕሮቴስታንቶችን ጭምር ባካተተው ሕዝባዊ ተቃውሞ ምክንያት ግራ የተጋባውና የተደናገጠው የአነግ ብልጽግና መንግሥት የሕዝቡን ተቃውሞ ለመገደብ በአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ሽፋን የወታደራዊ ዕዝ ወይም ጊዜያዊ አዋጅ(ኮማንድ ፖስት) በማስፈን የሕዝቡን እንቅስቃሴ እንዲገደብ አድርጓል።ምዕመናን የሰንበትን ጸሎት በቤተክርስቲያን እንዳያደርሱ ታግደው የተወሰኑ ቀሳውስት ብቻቸውን እንዲቀድሱ ሆነዋል። ባጃጅና ባለሁለት እግር መንኮራኩሮች እንዳይንቀሳቀሱ ተከልክለዋል፤የአዲስ አበባ ከተማ በጭርታዋ እንኳንስ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ቀርቶ በሽዎችም የሚቆጠር ሕዝብ የሚኖርባት ሞቅ ካለ መንደርም አንሳና ደብዝዛ የታዬችበት ጊዜ ነበር፤አሁንም ድረስ የወታደራዊው ጊዜያዊ አስተዳደሩ አልተነሳም።ይህ ሁሉ እያለ በከተማዋ የሚኖሩት የውጭ አገር ኤምባሲዎች ስላለው ሁኔታ ትንፍሽ አላሉም።የዬአገሮቻቸውም የዜና ተቋማት አልዘገቡም።ለነሱ ትኩረት የሚስበው የኢትዮጵያ ሕዝብ መጨፍጨፍ ሳይሆን በአገራቸው ከተማ መንገድ ላይ መኪና ለገጨው ውሻ ነው፤ያንን እንደ ትልቅ ዜና አድርገው ቀኑን ሁሉ ሲያደነቁሩ ይውላሉ።የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላትና ወዳጁን ያዬባቸው ጊዜያቶች ብዙ ቢሆኑም በቅርብ ከታዩት አንዱ ይህ የአሁኑ ነው።ሲጀመር ሥርዓቱን አቅፈውና ደግፈው ያስቀመጡት እነሱ በመሆናቸው ለምን ከሕዝቡ ጎን አልቆሙም የሚል ጥያቄ ማቅረብ የዋህነት ነው። ለሃያ ሰባት ዓመት ተላላኪያቸው ሆኖ ያገለገላቸው ወያኔ ተደብድቦ ሊጠፋባቸው ሲል በዓለም አቀፍ መድረኮችና የዜና አውታሮች ከተት ብለው ሲንቀሳቀሱ፣የእቀባ ጋጋታ ሲደረድሩ ታዝበናል።አሁን በደሉ የደረሰው እንዲጠፉ በፈረዱበት የኦርቶዶክስ እምነትና ሕዝብ ላይ ስለሆነ ዝምታቸው ሊደንቀን አይገባም።የኢትዮጵያ ሕዝብ በነሱ ላይ እምነትና ተስፋ ከማድረግና የነሱንም ቡራኬ ከመጠበቅ አገሩንና ነጻነቱን ለማስከበር የጀመረውን ትግል መልክና ቅርጽ አሲዞ፣ የጋራ አመራር ፈጥሮ መቀጠል ይኖርበታል።ይህ የተነሳሳ ሕዝባዊ እምቢተኝነትና ተቃውሞ በሽርፍራፊ መደለያ እንዳይዳፈን በንቃት መጠበቅ የሁሉም ድርሻ ነው።

በአገር ውስጥ ከሚያካሂደው ትግል ጋር ተያይዞ በውጭ አገር የሚኖሩት የቤተክህነቷ ምዕመናንና ቀሳውስት በመንግሥት ላይ የሚያደርጉት ተቃውሞና ለሕጋዊው ሲኖዶስ የሚሰጡት ድጋፍ ተቀጣጥሎ ሰንብቷል።በአውትራሊያ፣ በደቡብ አፍሪካ፣በካናዳና አሜሪካ፣በአውሮፓም ውስጥ ልዩልዩ ከተማዎች በእንግሊዝ፣ስዊድን፣በጀርመን፣ኔዘርላንድና ቤልጅዬም፣በመካከለኛው ምስራቅ በቤይሩት፣ በኢሚሬት ሳይቀር ብዙ ቁጥር ያለው አደባባይ ወጥቶ ድምጹን አሰምቷል።በነዚህ አገራት በተደረጉት ሰልፎች በአብዛኛው የቤተክህነት አባቶችን ትዕዛዝ የተከተለና ለመንግሥት ጥያቄ ከማቅረብ ባለፈ

ሥርዓቱን በፊት ለፊት የሚቃወም አልነበረም።የሴራውና የችግሩ ባለቤት መንግሥት ተብዬው መሆኑን የሚገልጹ ባይጠፉም ድምጻቸው በሌሎቹ አፍቅሮ አብይ የተዋጠ መሆኑን ወይም በሰልፉ ላይ ያልተገኙ መኖራቸውን መካድ አያስፈልግም።ከለዩላቸው የስርዓቱና የመንግሥት ደጋፊዎች በብዙ ቁጥር የሚበልጠው ፣የፖለቲካ ንቃትና ድፍረትም ያለው እውነተኛ ተቃዋሚና አገር ወዳድ መወገድ ላለበት ቡድን ጥያቄ አላቀርብም በማለት በሰልፉ ላይ ሳይሳተፍ ቀርቷል።እንዲሳተፍና የፖለቲካ ጥያቄና ተቃውሞ እንዲያሰማ በሰልፉ አዘጋጆች አልተፈቀደለትም።ፖለቲካና ፖለቲከኞች ወግዱ ተብለዋል። ገሃዱ ዓለም ግን ማንኛውም የህብረተሰብ ጥያቄ ከፖለቲካ ጥያቄ የሚወጣና የሚነጠል አለመሆኑን ባለፈው ሳምንት ጥንቅራችን በስፋት ሄደንበታል።በአገራችን ላይ ለደረሰው ሁሉ ተጠያቂው ከጎሰኝነት የፖለቲካ እምነት የሚመነጭ ስለሆነ ያንን የሚረታ የፖለቲካ አስተሳሰብና ትግል ያስፈልጋል።ያም ሆኖ ግን የተደረገው ሰልፍ በከፊልም ቢሆን የአብይን ቡድን በአደባባይ አጋልጦታል።በኢትዮጵያ ያሉት በሕዝቡ ግብር የተቋቋሙት የዜና አውታሮች ፋና፣ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት(EBC)ና ዋልታ የተባሉት በዝምታ ሲያልፉት ውጭ አገር ባለው የተቃውሞ ድምጽ መጉላት ምክንያት የውጭ አገሮቹ ቢቢሲና አልጀዚራ ሳይወዱ በግድ ሰፊ ሽፋን ሰጥተውታል።ከአገር ውስጥ ጋዜጠኞች ለሕዝብ ጥያቄ አጋርነታቸውን ያሳዩ ፣የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ የሆኑ የመንግሥት ዜና ተቋማት ሠራተኞች ምንም እንኳን ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ባሳዩት ወገንተኝነት ከሥራቸው ተባረዋል።ባለፈው ሳምንት ከገለጽነው ከአዲስ ቲቪ ዜና አንባቢ ከሳህለገብርኤል ይትባረክ ሌላ በዚህ ሳምንት የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዜና አቅራቢ በመሆን ለ15 ዓመት የሠራው በፍቃዱ አባይ የተባለው በኦርቶዶክስ እምነቱ ምክንያት ከሥራ ገበታው ላይ ተባሯል።እሱም ብቻ ሳይሆን የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የሆነው ፣በፖለቲካ ትንታኔው የሚታወቀው ቴዎድሮስ አስፋው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ደግፎ በመቆሙ ከቤቱ በአብይ አህመድ የኦሮሙማ አሽባሪ ተላላኪዎች ታፍኖ ወደ ፖሊስ እስር ቤት ተወስዷል። ልብሱን ለመልበስና የቤት ጫማውን ለመቀዬር እንኳን ዕድል አልተሰጠውም።በቢጃማ ሆኖ ልጁን አቅፎ በሚያጫውትበት ላይ አፋኙ ቡድን መኖሪያ ቤቱን ጥሶ ገብቶ አዋክቦ እንደወሰደው ቤተሰቦቹ ገልጸዋል። ከቀናት ቆይታ በኋላ በ30 ሽህ ብር ዋስትና እንዲፈታ ፍርድ ቤት ቢወስንም መፈታቱ ይፋ አልሆነም።የአነጋውያኑ የገንዘብ መዝረፊያ አንዱ ስልት እያሰሩ መጠዬቅ መሆኑን በተደጋጋሚ አይተናልና እንግዳ አይሆንብንም።ይህ በእንዲህ እያለ በከተማ ውስጥ የሚካሄደው አፈናና ድብደባ አልቆመም። ብዙ ወጣቶችና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሰባኪያን ታፍሰው በዬቦታው ባሉት የማሰቃያ ጉረኖዎች ተወርውረዋል።ከ2 ሽህ የማያንሱት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በተለም ወጣቶች በአዋሽ በረሃ በሚገኘው በሰሞኑ አጠራር የኢትዮጵያ ጓንታናሞ ተብሎ ወደተሰዬመው የማሳቃያ ቦታ መወሰዳቸው ታውቋል። የነሱም እጣ ፈንታ በገንዘብ ክፍያ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለን።

ይህ ማለት ያሰረውን ሁሉ በገንዘብ ይፈታል ማለት አይደለም፤በተራዘመ እስራት አሰቃይቶ የሚገላቸውም ሊኖሩ እንደሚችሉ መታወቅ አለበት።የፖለቲካ ጥያቄ ይዘው መንግሥት ሊገለብጡ ነው ያላቸውንና የሥርዓቱን ምንነት በድፍረት የገለጡትን፣ለአማራው ከአማራው በላይ የጮኸውን እንደ አንጋፋው ታዴዎስ ታንቱን አይነቶች በቀላሉ አይምራቸውም። ሕዝቡ በተለይም የአማራው ማህበረሰብ ለነዚህ ሊታገልና ነጻ ሊያደርጋቸው ይገባል።

ጠላትንና የትግሉን ይዘት ማወቅ የመጀመሪያ ጥበብ ነው። አባቶች ፊትለፊት ቀርበው ያቀረቡት ጥያቄያቸው እንዳልተመለሰላቸው እዬታወቀ በውጭ አገር በሚኖሩ ኤምባሲዎቹ በኩል በደብዳቤ የሚቀርበውን ጥያቄ ተቀብሎ የአብይ አህመድ ቡድን መልስ ይሰጣል ብሎ መጠበቅ ጅልነት ነው። ትግሉ ከአቤቱታ በላይ ነው።የሞት የሽረት ትግል ነው፤ አገር የማዳን ወይም የማጣት ትግል ነው። መዋቅራዊ የፖለቲካ ይዘት ያለው ፣መንግሥታዊ ሴራ ነው።ይህንን መካድ አያስፈልግም።

ትግሉን የፖለቲካ ይዘት የሚሰጠው ሌላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ሦስት አባቶች ያካተተ ቡድን ወደ ሩስያ መላኩ ነው።ይህ ቡድን ከሩስያ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ጋር ከመገናኘቱም በላይ የአገሪቱን መሪ ቪላድሚር ፑቲንን እንደተገናኘ በምስል የተደገፈ ዜና ወጥቷል። ታዲያ ከፑቲን ጋር ስለ አቶ ሳሪዎስ ሕገወጥ ቡድን ለመመካከር ብቻ ነው የሚል ብዥታ የለንም። የሩስያው ፓትሪያርክ የሚመሯትን የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲወክሉ ጎን ለጎን ፑቲን የአገሪቱን መንግሥት የፖለቲካ ክንፍ የሚወክል መሆኑ መዘንጋት የለበትም።የጳጳሳቱ ተልእኮ ሁለቱንም ወገኖች ማነጋገሩ ጉዳዩ የፖለቲካ ገጽ እንዳለው አመላካች ነው።ትግሉ ከሃይማኖት በላይ ነው የምንለውም ለዚያ ነው።የሲኖዶሱን ከሩስያ ጋር የመቀራረብ ሂደት ምዕራባውያን በዝምታ እንደማያልፉትና ጎራ እንደለዩ አብይ የሚመራው የኦሮሙማ ቡድን የሚያደርገውን አገር የመበተንና በሰባዊ ፍጡር ላይ፣ በተለይም የኢትዮጵያን አንድነት የሚያስከብር፣የውጭ ጣልቃ ገብነትንና ወረራን የሚጠላና የተከላከለ ብለው በጠላትነት በፈረጁት በአማራው ማህበረሰብ ላይ የሚደርሰውን ጭፍጨፋ በዝምታ ማለፋቸው አንዱ ማረጋገጫ ነው።

የአብይንና የሚመራውን የኦሮሙማ ቡድን ወንጀል ለመሸፋፈን የአገር ውስጥና የውጭ አገር የዜና ምንጮች የማይሄዱበት መንገድ፣የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም።አገር በቀውስ ስትናጥ፣ሕዝብ በኑሮ ውድነትና በርሃብ አለንጋ ሲገረፍ ደንታ የሌለው አብይ አህመድ ወለጋ ገብቶ የስንዴ ምርታማነታችን ተሳክቶ ለጎረቤት አገራት ከ3 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ልከናል ሲል ተቀብለው አስተጋብተዋል። በአሜሪካኖች መዳፍ የሚዘወረው የዓለም የገንዘብ ተቋም ደግሞ ኢትዮጵያ በኤኮኖሚ እምርታ ላይ ነች፣የወደፊቱም ከሰሃራ በታች ካሉት አገሮች ኬንያንም ጨምሮ በበለጠ የእደት ጉዞ ላይ መሆኗን የወጣው ጥናት ያሳያል ሲል ለስርዓቱ ሽፋን ሰጥቷል።የኑሮ ውድነት፣የሰላም እጦት፣ጦርነትና ግጭት መኖር፣ለእድገት ተጻራሪ መሆኑ በዓለም የገንዘብ ተቋሙ ተክዷል።የኦሮሙማው ቡድን በኢትዮጵያ መንግሥት ስም የሚሰበስበው እርዳታና ብድር የወያኔና የኦነግ ባለሥልጣኖች ከአበዳሪው ድርጅት ባለሥልጣኖች ጋር የሚቀራመቱት እንጂ ለእዳ ተሸካሚዋ ኢትዮጵያ የሚውል አይደለም።በኢትዮጵያ ስም ትግራይና ኦሮሚያ ለሚባሉ አገሮች ውልደት ለሚደረገው ወታደራዊ ዘመቻ፣ዝግጅት ስንቅና ትጥቅ የሚውል ገንዘብ ነው።የወለጋ ስንዴውም ሽያጭ ለዚያው ከባቢ ባለሥልጣናትና ባለሃብት እንጂ ለቀረው ያገሪቱ ዜጋ ቀርቶ ለደሃው ኦሮሞ ተወላጅ የሚተርፍ አይደለም።የሚተርፈው ነገር ቢኖር በስሙ ለተገኘው ዕዳ ከነወለዱ የመክፈል ግዴታ ብቻ ነው። በጦር ሜዳ እርስ በርሱ እንዲጫረስ የፕሮፓጋንዳ እስረኛ መሆኑ ብቻ ነው።

የአብይ አህመድ ሌላው ጉድ የተጋለጠው ጓደኛዬ ብሎ በሚጠራው በማክሮን አገር በፈረንሳይ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ አንባቢ ባለው እውቁ የሌ ሞንድ(LE MONDE) ጋዜጣ የወጣው ማጋለጫ ነው።ጋዜጣው አብይ አህመድ አሰራዋለሁ ላለው ቤተመንግሥትና የጫካ ዕቅድ(ፕሮጀክት) የተገለጸው 500 ቢሊዮን ብር ብቻ ሳይሆን ከዚያ በላይ ከ800 ቢሊዮን ብር እንደማያንስ በእቅዱ ዙሪያ ከሚሳተፍ ግለሰብ ያገኘሁት መረጃ ያረጋግጣል ብሏል።ይህ ሁሉ የአገር ሃብት ውድመት በኢትዮጵያ ፍርስራሽ ላይ ኦሮሚያ የምትባል አገር እመሰርታለሁ ከሚል እብሪትና ድፍረት የመነጨ ነው። ሕዝብ በዝምታ ተመልካች ሆኖ ከተቀመጠ የአገር አፍራሾቹ ህልም ገሃድ ይሆናል።

በሰሞኑ ዬታዩትንና የተሰሙትን ድብልቅልቅ ያሉ ሁኔታዎችን ስናጤን ያገራችን ፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳይ ለገናኘ ናዛዥ ያስቸገረ ፣መላ ቅጡ የጠፋው ሆኖ እናገኘዋለን።ጧት የተነገረው ማታ ላይ፣ከሰዓት በፊት የተነገረው ከሰዓት በኋላ እርስ በራሱ የሚቃረን ትርክት የምንሰማበት በመሆኑ የቱን ይዘን የቱን እንደምንለቅ ግራ ገብቶን ሰንብተናል።እኛም ብቻ ሳንሆን ምልአተ ሕዝቡ ተወናብዷል።ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል

ሰኞ የካቲት 6 ቀን 2015 ዓም አብይ አህመድ ከሕጋዊው ሲኖዶሱና ከሕገወጡ ቡድን የተውጣጡ 6 ጳጳሳትን በቤተመንግሥቱ ሰብስቦ ታርቀናል ብላችሁ ካልገለጻችሁ መከራው ለእናንተም ይተርፋል በሚል ማስፈራሪያ አግባብቶ በማግስቱ ማክሰኞ የካቲት 7 ቀን 2015 ዓም የቅርብ ባለሚሎቹንና በሽምግልና የታሰተፉትን ሰዎች አስከትሎ ጳጳሳቱን ይዞ ወደ ሕጋዊው ሲኖዶስ መንበር በመሄድ እራሱን ክርስቶስ አድርጎ የጠፋውን በግ ፈልጌ አኘኼቼ ይኼው መጥቻለሁ የሚል ትያትር ተጫውቶ የሰላምና የእርቅ አባት ሆኖ ቀረበ።ይህ ትያትር በስፋት በሚቆጣጠረው የዜና አውታር እንዲሰራጭ አድርጎ የሕዝቡን እንቅስቃሴ ለማለዘብ ቻለ።አንዳንዱም በተለይም በአምልኮ አብይ ተጠምቀው ግን በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ የደረሰውን እንቃወማለን ብለው የነበሩት እንደገና ተመልሰው ከዛው ጉሮኗቸው ገብተው አብይ ለዘላለም ማለት ጀመሩ።

የአገሪቱ ፕሬዚደንት ተብዬዋ ሳህለወርቅ ዘውዴ ከፓትሪያርኩ ፊት ቀርባ ሰላም በመውረዱ እንኳን ደስ አለን ስትላቸው ስለዬትኛው ሰላም ነው የምታወሪው?የጠዬቅነው ሳይመለስ፣ልጆቻችን እየተገደሉ፣ እየታሰሩ፣አፈናው ሳይቆም ምን ሰላም ወረደ ትያለሽ ሲሉ ቀልቧን ገፈው እንደመለሷት የተነገረው ከሰው ጆሮ ሳይጠፋ፣በኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ላይ የሚደርሰው ወከባና መከራ ካልቆመ ከሥልጣኔ እወርዳለሁ፣እኔም ኦርቶዶክስ ነኝ! አለች የሚል ማደናገሪያ ተሰራጨ።

ከነሳውሪዎስ ጋር ኮበለለ የተባለው  የዬሩሳሌሙ መነኩሴ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ ጠዬቀ የሚለው በምስል የታገዘ ዜና ባዬንበት ዓይናችን በማግሥቱ ተመልሶ ወደ ሳሪዎስ ድንኳን  ጠፍቶ ሄዶ ታፍኜ ነው አለ የሚል ወሬ ተናፈሰ።አሁን ላይ የመነኩሴውን መዳረሻ ባናውቅም ስሙን ግን ከምግባሩ በመነሳት በአባ ጅዋጅዌ ለመቀዬር ተገደናል።የጅዋጅዌው ጨዋታ በመነኩሴው ብቻ አልቆመም። በሕጋዊው ሲኖዶሱም በኩል ታይቷል።

በመጀመሪያው ላይ ጠንካራ አቋም ይዞ፣ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጦ፣ምዕመናኑን ለትግል ጠርታ፣ መስዋእትነትም ከፍለውላት፣በውስጥና በውጭ አገር ያሉት ምዕመናን ከዳር እስከዳር ጮኸውላት፣ ከሥራቸው ተባረውላት፣ጸጉራቸውን ተላጭተው፣አመድ ነስንሰው ጥቁር ለብሰው፣በጾምና በጸሎት እራሳቸውን አድክመውና ለፈጣሪያቸው አንብተው ከኦሮሙማው ሴራና በደል ለማዳን ቆርጠው የተነሱትን ክርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን ሙስሊሞችን ፣ ፕሮቴስታንቶችን፣አማኙንና አላማኙን ያካተተው ትግል በተድበሰበሰ መልኩ ለአብይ አህመድና ለሳሪዎስ ቡድን ፍላጎት መንበርከኩን ስናይ ባገራችን ላይ የወደቀው አዚማዊ መንፈስ የኦርቶዶክስ ተዋህዶንም መንበር ሳይበክላት እንዳልቀረ ለመገመት ተገደናል።

ከዚህ ከተደረሰበት ስምምነት ላይ ሰው ሳይሞት መድረስ በተቻለ ነበር።የሲኖዶሱ ቅድመሁኔታዎች ባልተቀመጡም ነበር።አሁን ላይ ተደረሰበት የተባለው ስምምነት በእኛ እይታና ግንዛቤ የአብይ አህመድ ኦሮሙማና የሚያሽከረክረው የሳሪዎስ ቡድን ሲጠይቀው የነበረው ተቀባይነት እንዳገኘ ነው።አብይ አህመድ ሁለታችሁም አባቶቼ ናችሁ ተናግራችሁ ችግሩን ፍቱ፣ባለው መሠረት መድረኩን አመቻችቶላቸዋል። የሕጋዊ ሲኖዶሱም ቀኖናው ተጥሷል፣ሕገወጦች ናቸው፣ዳግም ከመንበሩ ፊት አይቀርቡም፣ይቅርታ ቢጠይቁም እንኳን በፊት በነበራቸው ምድራዊ መጠሪያ እንጂ የቤተክህነትን ስያሜ ሊይዙ አይገባም፣መንግሥት ለደረሰው ውድመትና የሕይወት መጥፋት ተጠያቂ ነው፤ የሚለው ክስ ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን ተብሎ አልፏል፤ይባስ ብሎም አብይ አህመድን የእርቁና የሰላሙ ባለቤት፣ እንደቀድሞው የተከፋፈለችዋን ቤተመቅደስ አንድ ያደረገ....ወዘተ የሚሉ ሙገሳና ምስጋናዎች ከመቸራቸው ባለፈ በጣም የሚያሳዝነው ንጹሃን የሲኖዶሱን ጥሪ ተቀብለው በግፍ የተጨፈጨፉት በአብይ አህመድና በክልሉ መሪ በሽመልስ አብዲሳ መሆኑ ሲታወቅ ከተጠያቂነት ይልቅ የሰላም አባቶች ተደርገው ተቆጥረዋል፣ተመስግነዋል።ህይወታቸው ላለፈው ዜጎች ካሳ ወንጀለኛው መንግሥት ሳይሆን

ምዕመናኑ እንዲከፍሉ ሲኖዶሱ ወስኗል፣የታሰሩትም መንግሥት እያጣራ ይፍታ በማለት በመፈንቅለ መንግሥት ስም የመሰረተውን ክስና ውንጀላ እውቅና የመስጠት በሚመስል መልኩ ያሻህን አድርግ ብለውታል።ይህ ነው ገሃዱ እውነታ!።በጣም የሚያሳስበው ነገር ቢኖር ሲኖዶስ በወሰደችው አቋም ብዙ ምዕመናን እንዳያዝኑና እንዳይኮበልሉባት ነው።

ውሎ አድሮ የወጣው ሚስጥር እንደሚያመለክተው አብይ አህመድ ከሁለቱም በኩል ሶስት ሶስት ጳጳሳትን ሰብስቦ ባናገረበት ወቅት ችግሩ የፖለቲካ አይደለም፤ችግሩ የተፈጠረው በውስጣችሁ ባለ መርዝ በሚረጭ ምክንያት ነው፣መርዝ የሚረጨውን ካሶገዳችሁ ችግሩ ይፈታል።አሁን ያላችሁ ዕድል መስማማት ብቻ ነው፤ በማለት ምክር መሰል ትዕዛዝ ስላቀረበላቸው ተስማምተዋል።ይህንን ጳጳሳቱ አልነገሩንም።እዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባው መርዝ የሚረጭ በውስጣችሁ አለ ሲል በመካከላቸው መተማመን እንዳይኖርና በጥርጣሬ ለመከፋፈል የሄደበት የተንኮል መንገድ እንደሆነ ቀደም ሲል ሲኖዶሱን ለመከፋፈል እንደ አባ ማትያስ ሁኑ ሲል የረጫትን መርዝ ማስታወሱ የአብይን ገጸ ባህሪ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። በቤተክህነቱ ጽ/ቤት ያዬነው ሌላው ፣አብይ አህመድ ከነሳሪዎስና የሥልጣን አጃቢዎቹ ጋር ሆኖ በመጣበት ጊዜ ለአቡነ ማትያስ  በማጎንበስ ክብራቸውን ሲገልጽ ቆመው የነበሩትን አቡነ አብርሃምን  የእምነቱ ስርዓት በማይፈቅደው መልክ እንደ ሰፈር ጓደኛው ዘሎ ትካሻቸውን ማቀፉና እሳቸውም በደስታ መጠምጠማቸውን ታዝበናል።መስቀላቸውን መሳምና መሳለም በተገባ ነበር።ይህ በራሱ አቡነ አብርሃምን ከአብይ አህመድ ጋር የተለዬ ግንኙነት እንዳላቸው አድርጎ የሚያስቆጥርና ልዩነት ለመፍጠር የሚያገለግል ሆኖ አግኝተነዋል።በተጨማሪም እንደ ጥሩ ወዳጅ ቅረበውና እያባበስክ  ወደራስህ ሳበው በሚለው ፍልስፍናው  ሊጫወት የሞከረው ፈሊጥ ነው።

በስምምነቱ  ላይ የተጠቀሰው ዋና ነጥብ በኦሮሚያና በሌሎቹ ክልሎች አዲስ ጳጳሳት እንዲሾሙ የሚለው ሲሆን ዓላማውን ስንፈትሸው አሁን ያለውን ሲኖዶስ በድምጽ ብልጫ አሶግዶ የሚፈለገውን አይነት የክልሎች ፓትሪያርክና  ሲኖዶሶች እውን ለማድረግ ነው።ከሦስቱ በስተቀር የሌሎቹ በዳር የመቀመጣቸውም ምስጢር ገልጠን ስናዬው በዬቦታው ይመደባሉ ከተባሉት ውስጥ የሚካተቱ ለመሆናቸው ማስረጃ ነው።እነሱም ከያዝነው አንነቃነቅም እያሉ በመፎከር ላይ ናቸው።ጉዳዩ ባለቤቷን የተማመነች ፍዬል ላቷን ከውጭ ታሳድራለች ነው።አብይ አህመድ አንድ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣አንድ ፓትሪያርክ አንድ ሲኖዶስ አለ እንጂ አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ  የሚል አገላለጽ አልተጠቀመም።ይህ ማለት በቀጣይ ዓላማቸው ቢሳካና ኦሮሚያ፣ትግራይ የሚባሉ አገሮች ቢመሰርቱ እያንዳንዳቸው በአገሩ ስም የሚጠራ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተቋም ይኖራቸዋል ማለት ነው።ከረጅም እቅዱ አንጻር ስንነሳ ደግሞ የትም ይሁን የትም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት የማይኖርበት አደጋው ትልቅ ነው።የእስልምና ሃይማኖትም ቢሆን አይድንም። አብይ አህመድ በአሜሪካኖች የተጠመቀበት ልማታዊ ፕሮቴስታንት( Prosperity Gospel)ሁሉንም ያጠፋቸዋል። ይህንን እቅድ ምዕመናኑ ቀርቶ ሕጋዊ ሲኖዶሱ የተረዳው አይመስለንም።

በቤተ ክህነት ዙሪያ ይህንን ሲያደርግ በመከላከያውም እንዲሁ የተበታተነውንና በልዩ ልዩ ስም የሚጠራውን የኦሮሞ ታጣቂ ቡድን በአንድ እዝና ተቋም ለመመሰብሰብም ሥራው ተጀምሯል። ጃልማሮ፣ሸኔ፣ ኦነግ ለሚባሉት ለአንድ ዓላማ  ጫካና ከተማ ተቆጣጥረው፣እዬገደሉና እዬዘረፉ  ላሉት ቡድኖች የእርቅ ደብዳቤ በሽመልስ አብዲሳ በኩል ተልኮላቸዋል።ለይምሰል እንጂ ወትሮም ቢሆን ከክልሉ አመራሮች ጋር የተለዩ አልነበሩም።ትጥቁም ስንቁም ከኦሮሞ ክልል ባጀት የተመደበ ነው። በሰሩት ወንጀል ሳይጠዬቁ በሕጋዊነት የክልሉ መከላከያ ይሆናሉ፣መሪዎቹም የአዛዥነት ሹመትና ጥቅማ ጥቅም ያገኛሉ።ጨዋታው ይህ ነው።

በአብይ አህመድ የሚመራው  ኦሮሙማ ቡድን ይህንን በስከጀርባ እያራመደ በፊት ለፊት እናቴ!፤እምዬ! ኢትዮጵያዬ የሚል የማጭበርበሪያ ዘዴውን ይጠቀማል።

እኛ ግን እንላለን አብይ አህመድ በአጋሮቹ ታጅቦ እነሳውሪዎስን በፓትሪያርኩ  ፊት ማቅረቡና በፊት ለፊት ወንበር ላይ ተቀምጦ መታዬቱ

1 የሻከረ ስሙንና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወገዘ ድርጊቱን ለመለወጥ ተጠቅሞበታል፤በአገሪቱ ሰላም ስለሌለ ለአፍሪካ ህብረት ስብሰባ አንመጣም ብለው ያንገራገሩትን መሪዎች ለመሳብ ተጠቅሞበታል።

2 በአሁኑ ቤተክህነትን የማፈራረስ ሙከራው ያለውን ሃይልና ጉልበቱን ፈትሾበታል፤የሕዝቡን ስነልቦናም ተረድቶበታል።

3 በሕዝቡ ጥንካሬ አለመሳካቱን አጢኖ ለወደፊቱ በበለጠ ዝግጅትና ስልት ያቀደውን የኦርቶዶክስ ተዋህዶንና የኢትዮጵያን ማፈራረስ ፍላጎቱን ለማሳካት እንዲዘጋጅበት ዕድልና ተመክሮ ሰጥቶታል፣

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ግን ያስገኘላት መልካምና አዲስ ዕድል የለም።በሲኖዶሱ ላይ አንዣቦ የነበረውን የመገልበጥ አደጋ ለጊዜውም ቢሆን ከማሶገዱ ሌላ፣የወደሙባትን መልሳ ለመጠገን ከሚደርስባት ወጭ፣ልጆቿን በሞት ከመነጠቅ፣ሊያፈርሷት የሞከሩትን እንደገና በብብቷ እንድታቅፍና ለዳግም ጥፋት ከመጋለጧ የተለዬ ትርፍ አላገኘችም።ከሁሉም በላይ ግን ተአማኒነቷ ከጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጓታል።

ምንም እንኳን ጉዳዩ የእምነቱ ተከታይ የሆነውን ሕዝብ፣እኛንም ጨምሮ የሚመለከት መሆኑን ብናውቅም በሃላፊነት የተመደበው ሲኖዶስ በመሰለው መንገድ ጉዳዩን የማስተናገዱን ሃላፊነት ለጳጳሳቱ ትተነዋል።ከሃይማኖት በላይ ለሆነው የአገር ህልውና፣የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ሁሉም አገር ወዳድ ሳይዘናጋ ፊቱን እንዲያዞርና ትግሉን እንዲቀጥልበት የተለመደ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። አሁንም ዜጋ በማንነቱ እዬተጨፈጨፈ ነው።ከጎጃምና ከወሎ በኩል የሚመጣው ኢትዮጵያዊ በተለይም አማራው  ወደ አገሩ ዋና ከተማ ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባ በመንገድ ላይ ታግቶ ለመከራ ተጋልጧል።ለህክምናና ለፍርድ ቤት ቀጠሮ የሚጓዘው በመንገድ ላይ ህይወቱ እንዲያልፍ፣ቀጠሮው ተሸሮ ፍርድ እንዳያገኝ ሆኗል።በሌላው አካባቢ በተለይም  ሸራርፈው የኦሮሞ ክልል ብለው በአዲስ ስም በሚጠሯቸው ቦታዎች  ለዓመታት ይኖር የነበረው ዜጋ ቤቱ እዬፈረሰ፣ንብረቱን እዬተወረሰ ባዶ እጁን ቀርቷል፤ሜዳ ላይ ፈሷል።የመንግሥት ያለህ ቢልም ሰሚ አላገኘም።መጠለያ አጥቶ ለብርድና ለስቃይ የተጋለጠው ደሃ ሕዝብ ህጻናት ልጆቹን በአውሬ እዬተነጠቀ ነው።በአዲስ አበባ በቅርብ እርቀት ላይ ከ9 የማያንሱ ሕጻናት በጅብ ተበልተዋል።መከራውን መቋቋም ያልቻሉትም ተስፋ በመቁረጥ እራሳቸውን እስከ ማጥፋት ደርሰዋል።

በሰበታና በአካባቢው ለረጅም ዓመታት ኖረው፣ወልደውና ከብደው፣በኢትዮጵያዊነት መስተጋብር ተሳስረው በጉርብትና የኖሩት  ዜጎች የአማራ ጎረቤቶች ናችሁ ተብለው እንደ አማራው ቤታቸው በግሬደር ተደምስሷል።ሥርዓቱ ማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ማንም ከአማራው ጋር እንዳይገናኝ ብቻም ሳይሆን ለሚደርስበት ጥቃት ሁሉ አማራውን ምክንያት አድርጎ እንዲነሳበት ለማድረግ ነው።

ለዓመታት የሰው ልጅ ሲጨፈጨፍ ፣የገዛ ልጁ ሲገደል ዝም ብሎ መቀመጡ ከምን እንደመጣብን አይታወቅም።በሌሎች አገሮች ማህበረሰብ ቀርቶ አንድ ግለሰብ ብሶት ሲደርስበበት አገር ይነቃንቃል፣ መንግሥትን ያባርራል፣ባለሥልጣኖችንም ለፍርድ ያቀርባል።ከ12 ዓመት በፊት በቱኒዝያ ተጀምሮ

ሌሎቹን የአረብ አገራት ያጥለቀለቀውን ሕዝባዊ እምቢተኝነት ያስከተለውን የአምባገነኖችን መንግሥታት መንኮታኮት ማሰቡ በቂ ነው።

የአማራው ክልል የተባለው አካባቢና ሕዝብ ለወያኔና ለኦነግ ዳግማዊ ጥምር ወረራ ተጋልጦ ይገኛል። የጉራጌ ማህበረሰብ ሕገመንግሥታዊ መብቱን በመጠዬቁ በውሃ ጥም እንዲያልቅ ተፈርዶበታል።ያንን ለመቃወም ባዶ ባልዲ ይዞ እባካችሁ ሬሳ የማጥብበት እንኳን ልቀቁልኝ፣በስሜ ብዙ ሚሊዮን ብር ወጭ ሆኖ ከተሰራው ማጠራቀሚያ ውሃ የማግኘት መብቴ ይጠበቅልኝ በማለቱ በስርዓቱ ታጣቂዎች የጥይት ናዳ ወርዶበት ንጹሃን ልጆቹን በሞት አጥቷል፤ብዙዎቹም ቆስለዋል።ይህ ሁሉ የተደረገው የጉራጌ ማህበረሰብ የክልል መብቱ ከታወቀ የኦሮሙማው አገር ምስረታ ሊኖር የሚገባው አንድ ወጥ የመሬት ስፋት ሊሰናከል ይችላል ከሚል ስጋት የመነጨ መሆኑን የከባቢው ፖለቲከኞች ይናገራሉ። እርግጥ ነው ጉራጌው ክልል ሆኖ በመሃል ከተቸነከረ የኦሮሙማው የከፋና ጅማ ከባቢን ለመጠቅለል አዳጋች ሊሆንበት ይችላል።

በሌላውም በኩል የደቡብ ወሎ ሙስሊሞች የኦሮሙማው ስርዓት መጅሊሳችንን ለመስበርና እኛንም ለመዋጥ እዬተንደረደረ ብዙ ጉዳት አድርሶብናል ሲሉ አደባባይ በመውጣት ተቃውሟቸውን በማሰማት ሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪ አድርገዋል።ወሎን በአካባቢ ሰነጣጥቆ ለመዋጥ የኦሮሙማውና የወያኔ ቅድመ ዝግጅትና ፍላጎት ስለሆነ እንግዳ ነገር አይሆንም። የሙስሊም ወገኖቻችንን ጥሪያቸውን ሰምቶ ከጎናቸው መቆም ለሙስሊም የእምነት ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ አካል የሆነውን ወሎንና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳን ስለሆነ ሁሉም ከጎናቸው እንቁም የሚለው የእኛም ጥሪ ነው።

አሁንም ቢሆን ስምምነት ተደረሰ ከተባለበት ቀን ወዲህ በአዲስ አበባ የማሳደድና የማዋከቡ ፣ በወለጋም የመግደሉና የማፈናቀሉ ተግባር እንደቀጠለ ነው።አብይ አህመድ ፊት ለፊት ሲያደነዝዝ የኦሮሙማው ቡድን የሸብር ተግባሩን በጫካና በከተማ ተያይዞታል። ይበልጥ እልህና ንዴት በተቀላቀለበት ስሜት እዬፈጸመው ነው።

ሕዝቡ ለመብቱና ለነጻነቱ፣ለአገሩም አንድነት የሚያደርገውን ትግል ሊቀጥልበት ይገባል። በጾምና በጸሎት ብቻ ተወስኖ መቀመጥ የለበትም።ጾምና ጸሎት ለትግሉ የመንፈስ ብርታትን ሊሰጥ ይችል ይሆናል እንጂ ችግሩን አይፈታውም።ችግሩ የሚፈታው የችግር ባለቤቱን ሲያሶግዱት ብቻ ነው።የኦነግ መራሹን የጎሰኞች ስርዓትና አጋሩን የወያኔ ቡድን ማሶገድና በአገር ወዳድ መንግሥት መተካት ብቻ ነው።ለዚያ በሰላማዊ ትግሉ መቀጠል ግድ ይላል።ለመጀመር ያህል ለተወሰኑ ቀናት በቤት ውስጥ የመቀመጥ አድማ ቢመታ ቀላል የማይባል ውድቀት በስርዓቱ ላይ ሊያደርስ ይችላልና እንዲታሰብበት ለማሳሰብ እንወዳለን። ይህንን ለማድረግ ተራው በአርምሞ ውስጥ የቆዩት የፖለቲካ ድርጅት ነን ባዮችና የብዙሃን ማህበራት ናቸው። የታመቀው ሕዝባዊ ትግል ገንፍሎ ለመውጣት ከጫፍ ላይ መድረሱን ባለፉት ቀናቶች አይተናል። ሙሉ ለሙሉ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚችል ሃይል መሆኑንም አሳይቷል።ይህንን ግዙፍ ሃይል ይዞ መንቀሳቀስ ለለውጥ ቆሜያለሁ የሚለው ሃላፊነትና ድርሻ ነው።

ሕዝባዊ ትግሉን ለማዳከምና ለመከፋፈል በመንግሥት በኩል ብዙ መደለያ ስራዎች በመሠራት ላይ ናቸው።የመምህራኑን የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ በተወሰኑት ላይ ብቻ ተግባራዊ ሆኗል።ለዩኒቨርስቲ ሊቀሊቃውንቱ (ፕሮፌሰሮች)እስከ ስምንት ሽህ ብር በዬወሩ ጭማሪ ሲደረግ ለመደበኛ መምህራን (ለሌክቸረር) ደግሞ 1800 ብር በወር ተጨምሯል።ብዙሃኑ መምህር አፍንጫህን ላስ ተብሏል።

በተመሳሳይም በኦነጋዊት አዳነች አቤቤ የሚመራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በስሩ ላሉት የመስሪያ ቤት ሃላፊዎችና የክፍለከተማ አስተዳዳሪዎች በወር 15,000 ሽህ ብር ሲጨምር እንደ ሥልጣን እርከኑ ከ2,500 እስከ 1,500 ብር ድረስ ጭማሪ ተደርጓል።ሌላው ችግሩ ይበልጥ የሚጠብሰው ብዙሃኑ ዝቅተኛ ሠራተኛ የበይ ተመልካች እንዲሆን ተፈርዶበታል።በዚህ ልዩነት በመምህራኑና በሠራተኛው መካከል ጭቅጭቅ ፈጥሮ ሲነታረኩ የአገር ነኩን ትግል መስመር ለማሳት ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል።ከደመወዝ በላይ የአገር መኖር ይበልጣል፤አገር ሳይኖር ገንዘብ፣ሥልጣንና ሃብት ትርጉመ ቢስ ነው።ጅንጀሮም መጀመሪያ የመቀመጫዬን ብላለችና ከሁሉም በፊት በሰላምና በአንድነት እንዲሁም በእኩልነት የምንኖርበት አገር ይኑረን።

የዬካቲት ወር ትርጉሙ መክተት፣ከተተ ሲሆን ወቅቱ የበልግ ጊዜ ስለሆነ ፣ሰብልን አጭዶና ወቅቶ አበጥሮ ሰብስቦ ከጎተራ አስገባ ማለት ነው። በማህበረሰብም ደረጃ የተከሰተውን ችግር ለመፍታት ወቅቱ መሆኑን ያሳያል። የዛሬ 49 ዓመት የዬካቲቱን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የሚደግም ሁኔታ ተፈጥሯልና የተዝረከረከውን ሕዝባዊ ትግል በአንድ የትግል ቋት ስር ሰብሰብ አድርጎ ለመታገል ያለውን አጋጣሚ መጠቀሚያው ጊዜ አሁን መሆኑን ያመላክታል።ያንን ተረድቶ ጊዜውን መጠቀም ብልህነት ነው። ለመጠቀም አለመቻል ደግሞ በዋዛ ፈዛዛ ለቀጣይ ብዙ ዓመታት የባርነትን ቀንበር ለመሸከም ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው።ከዚያም በላይ አገር አልባ የመሆንን እጣ ፈንታ ለመቀበል መወሰን ማለት ነው።

ይህንን ጽሑፍ በማዘጋጀት ላይ እያለን ይሆናል ብለን የሰጋንበትን ወሬ ሰምተናል።ያም አፈንጋጩ የሳሪዎስ ቡድን ከመንበረ ጳጳሳቱ ግቢ ወጥቶ ባልታወቀ ቦታ ሦስት ቀናት ከተደበቀና ከኦሮሙማው ቡድን ሲመካከር ቆይቶ ሁሉም ሕዝብ የተደሰተበትን ስምምነት እንዳልተደረገ የሚገልጽ መግለጫ መስጠቱን ነው።በአሁኑ መግለጫውየኦሮሞና የብሔር ብሔረሰቦች ሲኖዶስ በሚል መጠሪያው ሳይሆን አዲሱ ሲኖዶስ በሚል መጠሪያ ነው።በዬቀኑ መጠሪያ ስሙንና ጥያቄውን እዬለዋወጠ መምጣቱ ቡድኑ ምን ያህል ወራዳ፣የማይታመንና ይሉኝታ ቢስ መሆኑን ያሳያል።ዓለም በፊት ለፊት ጉልበት ስሞ፣ ጥፋቱን አምኖ መመለሱን ማዬቱን ከዶ፣የፈረመበት ሰነድ ቀለሙ ሳይደርቅ ብቅ ማለቱ በስሙ የሚጠቀምበት ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ መንገድ የክርስትና እምነት ተከታይ የሆነው ሁሉ የሚያፍርበትና አንገቱን የሚደፋበት ድርጊት ነው።ነገሩ ሁሉ ከሃይማኖት በላይ ነው የምንለውም ለዚያ ነው።ኦነጋውያን ያሰቡት ዓላማ የሚያጨናግፍባቸው ከመሰላቸው አንድና ሁለቴ ሳይሆን መቶ ጊዜ ቢክዱና ቃላቸውን ቢያፈርሱ አይከብዳቸውም።በውሸት ትርክት ተጠምቀውና ተክነው ያደጉበት ስለሆነ ጥረታቸው ውሸትን በማሻሻሉና በማሳደጉ ላይ እንጂ እውነትን በመቀበሉ ላይ አይደለም። ከላይ ጌታዋን የተማመነች ፍዬል ላቷን ከውጭ ታሳድራለች ብለን ያልነውም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ነው።መግለጫውን ከሰጡ በኋላ በወጡ በሶስተኛው ቀን አርብ የካቲት 10 ቀን 2015 ዓም ከሰዓት በኋላ እንደ ድል አድራጊ በሲኖዶሱ መንበረ ግቢ በተሰጣቸው መኖሪያ ቤት ገብተዋል።ይህ ትእቢታቸው በቀጣይ ለሚነሳው ችግርና ውዝግብ አይዞህ ባይ እንዳላቸው ያመላክታል።ያም የአብይ አህመድ የታጠቀ የኦነግ ወታደር ነው።እርምጃውም ሕጋዊ ሲኖዶሱን በሃይል አሶግዶ የነሳሪዎስን ቡድን በመንበሩ ላይ ማስቀመጥ ይሆናል፤ያ ከሆነ ደግሞ ወደ ለዬለት አገራዊ ብጥብጥና ቀውስ ይከተናል ብለን እንሰጋለን።ለማንኛውም ግን ለመግደል ሳይሆን ላለመገደል መዘጋጀትና መጠንቀቅ ካለብን ጊዜ ላይ ደርሰናል።ቀውሱን ስፖንሰር ያደረገው የአብይ አህመድ መንግሥት በቀጣዩ የሚወስደው እርምጃ ካለ ሂደቱን ግልጽ ያደርግልናል።ስለሆነም እነሳሪዎስ በቤተሲኖዶሱ ግቢ

ቤተክህነት ቀኖናዋን ተከትላ፣የይቅርታ እጇን ዘርግታ ላሳዬችው ፍቅር መልሱ ይህ ከሆነ የሚጎዳው ከሃዲው ወገን እንጂ ተከጅዋ ቤተክህነት አይደለችም።ለማንኛውም ጥርጣሬና ትዕግስት አብረው እንደሚሄዱ የተማርንበት አጋጣሚ ነው።ያልጠረጠረ ተመነጠረ ተብሏልና! ስለሆነም እነሳሪዎስ በቤተ

ሲኖዶሱ ግቢ ሲገቡ በቀሚሳቸው ስር መሳሪያ ይዘው የመግባት አጋጣሚ ስለሚኖርና ለቀጣዩ እርምጃ ተኩስ በመከፈት የሚጠባበቀው የኦነግ ታጣቂ ገብቶ ሕጋዊ ሲኖዶሱን በማሶገድ የነሳሪዎስን ቡድን በመንበሩ ላይ ለማስቀመጥ ይንቀሳቀሳል የሚል ስጋትና ጥርጣሬ አድሮብናል።

አርብ የካቲት 10 ቀን 2015 ዓም የሕጋዊ ሲኖዶሱ ተወካዮች አቡነ ጵጥሮስና አቡነ አብርሃም ያለውን ሁኔታ በሚዲያ ቀርበው ማብራሪያ ሰጡ።ይህ በእንዲህ እያለ ጉድ ጉድ ስንል በማግስቱ በአብይ አህመድ ትዕዛዝ የነ ሳሪዎስ ቡድን ወደ ሕጋዊው ሲኖዶስ መመለሱንና እውቅና መስጠቱን በነዚሁ ጳጳሳት በኩል ሰማን።የጉድ አገር ገንፎ እያደር ይፋጃል የሚለው ምሳሌ ትዝ አለንና የአገራችን ፖለቲካ ገና ብዙ ትያትር የምናይበት መድረክ በመሆኑ ቀጣዩን በጉጉት እንጠብቃለን።ለዳግመኛ ክህደት በዝግጅት ላይ እንዳሉ ግን ጥርጣሬያችን ከፍተኛ ነው።አገር ለማፍረስ የተነሳ እንዲህ በቀላሉ አይመለስም።

አብይ አህመድ ገጸ ባህሪውን ለመሸፈን ከአቡነ ማትያስ ጎን ተቀምጦ የተነሳው ፎቶ ግራፍ ሲገርመን በቅዳሜው እለት በየካቲት 11 ቀን 2015 ዓም እሳቸውንና አቡነ ጴጥሮስን አስከትሎ በአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ አድርጓቸዋል።ያስተላለፉት መልእክት ክፋት ባይኖረውም ዬተጠቀሙበት ቋንቋ ያገራችንን ማንነት በሚገልጸው ፣በብሔራዊ ቋንቋችን በአማርኛ አለመሆኑ ሥርዓቱ አማርኛንና አማራ ነክ፣ኢትዮጵያዊነት ያለውን ሁሉ ከማጥፋት ዓላማው አንጻር ለዚያ መሣሪያ በሚያደርጋቸው በውጭ አገር ቋንቋ ፣በእንግሊዝኛ መናገራቸው ያሳዝናል።አፍሪካንያኑ እንዲረዱት ታስቦም ከሆነ እንደማንኛውም ጊዜ የትርጉም ማዳመጫ ሊጠቀሙ ይችሉ ነበር።የለም እንዳይባልም የዛሬ 60 ዓመት ሲጀመር ጀምሮ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ተሟልቶ ይገኛል።

በዚህ ብሰባ ላይ አብይ አህመድ እንደልማዱ ብዙ ዘላብዷል፤ቀባጥሯል።የራሷ እያረረባት የሌላ ታማስላለች እንደሚባለው በሱ አመራር የኢትዮጵያ አንድነት ለመፈራረስ ጫፍ ላይ ባለበት፣ዜጋ በጎሳ ማንነቱና በሚከተለው እምነት ሲጨፈጨፍ፣ሲፈናቀል፣በርሃብና በበሽታ ሲረግፍ ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ በሚመስል መልኩ ከራሳችን አልፈን የሌሎቹን ጎረቤት አገራት ሰላምና አንድነት አስጠብቀናል፣ እራሳችችንን ከመመገብ አልፈን ለሌላው አገር ስንዴ ለመላክ ችለናል፤የአፍሪካን ችግ በአፍሪካውያን የሚለውንም መርህ በተግባር ተርጉመናል ሲል አዳማጮቹን ከውስጣቸው ሳያስቃቸው እንደማይቀር እርግጠኞች ነን።መቼም አመድ በዱቄት አይስቅም ሆኖ እንጂ ደፋርማ ያፍሪካ መሪ ቢኖር፤ያለውን ሁኔታ በፊትለፊት ገላልጦ ባቀረበና የውጭ አገር መንግሥታት አሜሪካ፣አውሮፓና የመካከለኛው ምስራቅ የሚያሽከረክሩት ስርዓት እንደሚመራ በነገረው ነበር።ብቻ ሁሉም ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ብሎ አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ ላለመሆን በጭብጨባ ሸፍኖት አልፏል።

በቀጣዮቹ ቀናት ምን ሊከሰት እንደሚችል በስጋት ላይ ሆነን በመጠባበቅ ላይ ነን።

ሕዝባዊ ትግሉ ይቀጣጠል፣ለዳግማዊ የካቲት እንሰለፍ!

የሁሉም አይነት ችግርና ቀውስ ምንጭ የሆነው የጎሰኞች ሥርዓት ይደምሰስ!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!